*"... ከስድስት ዓመታት በፊት ለምሠራበት ጋዜጣ ጀማሪ ሪፖርተር በመሆኔ፣ እንደነባር ጋዜጠኞቹ በእርማት ሥራ ባልጠመድም፣ ዲዛይን ተሠርተው ያለቁ ጋዜጦችን፣ አራት ኪሎ ወደሚገኘው ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት ማድረስ ግን አልፎ አልፎ የሚገጥመኝ የሥራ ድርሻዬ ነበር። ሃያ ሁለት አካባቢ ከሚገኘው ቢሮዬ አራት ኪሎ ደርሼ ስመለስ፣ ተራርቀው የሚቆሙ የመንገድ ላይ ዝሙት አዳሪዎች፣ እስኪነጋ ከመመልከት ውጭ እንደ ዘንድሮው በድንግዝግዝ ብርሃን ሥራ የሚጀምሩትን ማየት ግን አልገጠመኝም ነበር ..." የምትለን የጋዜጣችን ዘጋቢ **ጽዮን ግርማ፣** ከጎዳና ሴተኛ አዳሪዎች ጋር ባሳለፈቻቸው ሦስት ሌሊቶች፣ የአንበሳ አውቶብሶችና ሚኒባስ ታክሲዎች፣ ቤት አዳሪዎችን ገና ወደ መንደራቸው ሳይደርሱ ዝሙት አዳሪዎች ለሥራ የሚወጡበትን ምሥጢር አጫውተውናል ትለናለች።*

# ሦስት ሌሊቶች ከጎዳና ዝሙት አዳሪዎች ጋር

በሥነ ኅብረተሰብ ጥናት ዝሙት አዳሪነት ቀዳሚ ሞያ (the oldest profession) የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፣ በቅርብ ዘመናት በተለይም ባደጉት ሀገሮች ቦታ ተለይቶለት የገቢ ግብር የሚከፈልበት፤ ትልቅ ኢንዱስትሪ ለመሆን በቅቷል። በሀገራችን ደግሞ በየጊዜው በተፈጠሩት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ሳቢያ እየተባባሰ የመጣው ዝሙት አዳሪነት፣ ከተወሰኑ መንደሮች ወደ አውራ ጎዳናዎች ገንፍሎ የወጣበትና የሚያሳፍርበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

የቀኑ ክፍለ ጊዜ ተሰማሪዎች፣ ከተማውን ለምሽተኞቹ ለቀው ለመኝታ ሲሰማሩ፣ ጥቂት የሌሊት ሥራ በሚያሰሩ ፋብሪካዎች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ፈጣን ምግብ በሚሸጡ ሱቆች ... ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች ደግሞ ወደየሚሠሩበት ቦታ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ተጠቃለው ይገባሉ።

"ቅርብ" በሚባሉ ጊዜያት ደግሞ እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት፣ ጭር እያለ በሚሄደው የአዲስ አበባ የምሽት ጎዳና ላይ፣ ዕድሜያቸው 14 እና 15 ዓመት የሚሆናቸው ሕፃናት ለዝሙት አደርነት ብቅ ማለታቸው ብዙም አስገራሚ አልነበረም።

መቀመጫቸውን በቅጡ ያልሸፈነ ብጣቂ ጨርቅ አገልድመው፣ እንብርታቸውን ለምሽቱ ብርድ አስረክበው፣ ታክሲ ጠባቂ መስለው የሚቆሙ የጎዳና ላይ ዝሙት አዳሪዎችን ገና የምሽቱ ሦስት ሰዓት እንኳ ሳይጠጋ ማየት ሰሞነኛ ሆኗል።

ከስድስት ዓመት በፊት ለምሠራበት ጋዜጣ ጀማሪ ሪፖርተር እንደመሆኔ እንደነባር ጋዜጠኞቹ በእርማት ሥራ ባልጠመድም፣ ዲዛይን ተሠርተው ያለቁ ጋዜጦችን፣ አራት ኪሎ ወደሚገኘው ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት ማድረስ ግን አልፎ አልፎ የሚገጥመኝ የሥራ ድርሻዬ ነበር። ሃያ ሁለት አካባቢ ከሚገኘው ቢሮዬ አራት ኪሎ ደርሼ ስመለስ ተራርቀው የሚቆሙ የመንገድ ላይ ዝሙት አዳሪዎች፣ እስኪነጋ ከመመልከት ውጭ እንደዘንድሮው በድንግዝግዝ ብርሃን ሥራ የሚጀምሩትን ግን ማየት አልገጠመኝም ነበር። የጎዳና ላይ ዝሙት አዳሪዎች ገና ቀኑና የምሽቱ አየር በቅጡ ሳይቀላቀሉ በጊዜ ሥራ ሊጀምሩ የቻሉበትን ምክንያት ለማወቅ ሦስት የተለያዩ ለሊቶችን ከነሱ ጋር አሳለፍኩ።

"... ብዙም ሥራውን ሳትለመጂ በአንድ ጊዜ፣ ከቦሌ መጀመሩ ሊከብድሽ ይችላል፤ ሰሞኑን ደግሞ ሥራ ስለቀዘቀዘ እንኳን ለጀማሪ ለእኛም እየከበደን ነው፤ በዚህ ላይ ሲያዩሽ ምንም ..." ብላ ሃሳቧን ሳትጨርስ፣ ከመጫሚያዬ

እስከ ፀጉሬ ተመለከተችኝ፤ ሁለት ሰዓት ተኩል ሳይሆን ነበር ቦሌ መጨረሻ በተለምዶ "ብራስ" እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ቆማ የምሽቱን ሥራ ገና ከመጀመሯ "እዚህ አካባቢ ገበያ ይኖራል? ጀማሪ ነኝ" ብዬ አጠገቧ ቆም ስል ብዙም ያልተደሰተችው ትጊ መልስ የሰጠችኝ።

በፈረንጆቹ ቀለም ፀጉሯን አቅልታ ጭብርር አድርጋዋለች፤ ሳሳና ወደጎን ሠፋ ያለ አጭር ቡኒ ቀሚስ ለብሳለች፤ ከላይ ለአመል ጣል ያደረገቻት አላባሽ ሰውነቷ ላይ ተጣብቃ ለተስተካከለው የሰውነት ቅርጿ አስተዋፆኦ አድርጎላታል። ቀረብ ብዬ ሳያት ፊቷን በሜካፕ ለምሽቱ እንዲስማማ አድርጋዋለች። ስልችት ባለ አተያይ አየት አደረገችኝና ቦታም ሳትሰጠኝ በትከሻዋ ካነገበችው ትልቅ ቦርሳ ሲጋራና መለኮሻ አውጥታ ታጨስ ጀመር። "ማስቲካ አለሽ?" የተጀመረው ወሬ እንዳይቋረጥ ማግባቢያ ነበር።

ከጥርስ ውስጥ የማትወጣ ቁራጭ ማስቲካ ሰጠችኝ። ብዙም ሳላዋራት 70 ሜትር በሆነ ርቀት ላይ የቆሙ ሌሎች ሁለት ሴቶች "ዛፓዎች መጡ" አሉና ጨለማ ውስጥ ገቡ።

ሁለት ፖሊሶች ወደቆምንበት ተጠጉ፤ "እሙ ታክሲ አጥተሽ ነው?" በቀጥታ ለኔ የተወረወረ ጥያቄ እንደሆነ ቢገባኝም መልስ አልሰጠሁም። "አንቺ ጃርት እንዲህ ዓይነት ልብስ አትልበሺ አላልኩሽም? ስመለስ እዚህ ጋር ባገኝሽ ሽባ ነው የማደርግሽ" አላት አንዱ ፖሊስ ወደእሷ ዞር ብሎ ለማስፈራሪያ "እሺ" የሚል ቃል ከአፏ ሳይጠፋ ተለማምጣ አሳለፈችው።

"ለምንድነው ፖሊሶቹ እንዲህ የሚያሯሩጡትና የሚሳደቡት?" ስል እንደገና ጠየቅኋት፤ "ሳይሄዱ እነሱኑ ብትጠይቂያቸው አይሻልሽም?" ስትል ከገላመጠችኝ በኋላ ምን እንደተሰማት ባላውቅም፣ መልሳ መልስ ሰጠችኝ "በቃ ከምድረ ገጽ አጥፋቸው ብሎ አለቃቸው አዟቸዋል ብቻ አላሠራ ብለውናል ሲያባርሩን ነው የሚያድሩት"፤ ሲጋራዋን መሬት ጥላ፣ በእግሯ እርግጥ አደረገችና ተቻኩላ ወደ መንገዱ ወጣች። መቼም ያየኋቸውን ለድርድር የሚመጡ ይሁን አውቀው መኪኖች ታርጋ ብናገር ስንቱን ከስንቱ እንደማጣላ እየታሰበኝ፣ አቁሞ የሚያናገራት ባለ ቀይ ቶዮታ ኮሮላ መኪና ታርጋ ላይ ዓይኔን ወረወርኩ። ስላልተሳካላት በግማሽ ልቤ እያዘንኩ የጀመረችውን ሳትጨርስ ጥላኝ ባለመሄዷ ደስ አለኝ።

ሲጃራዋን እንደገና ለኮሰችና ጥሏት የሄደውን ባለቶዮታ የስድብ መዓት አወረደችበት፤ "ሳትስማሙ ቀራችሁ?" አልኳት፤ ስድቡ ቀጠለ። "ፖሊሶቹ ግን ከማባረር ውጭ ምንም ርምጃ አይወስዱም?" ምን ዓይነት ርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ ጠቆመችኝ። "ይደበድባሉ?" ጥያቄዬ አሰለቻት መሰለኝ፤ "ወይ በገንዘብ ወይ በዓይነት ትሰጫለሽ፣ ሁለቱንም ተቀባይ ካጣሽ ደግሞ ጠያቂ አግኝተሽ እንቢ ካልሽ ጣቢያ ታድሪያለሽ በማግስቱ ጠዋት ትፈቻለሽ" የገንዘቡስ እሺ በዓይነት የሚሰጠው የሌሊት ጉቦ ምን እንደሆነ እንድታብራራልኝ ጠየኳት።

ስሟን ጠይቄ "ትጊ" መሆኗን ከነገረችኝ በኋላ ብዙ ብናወጋም በየመሃሉ ግን ሥራዋን አትረሳም፤ መኪና በመጣ ቁጥር ሰውነቷን ነቅነቅ እያደረገች ወደ አስፋልቱ ትወጣለች። ሥራ ከጀመረች ሁለት ዓመት ሆኗታል፤ ከማክሰኞ እስከ ቅዳሜ ትሠራለች፣ እሁድና ሰኞ ግን የዕረፍት ቀኖቿ ናቸው። ገላዋን ሽጣ ማደር የጀመረችው ቡና ቤት ውስጥ ነው፤ የቀድሞውን አማርራ የአሁኑን "ይመስገን!" ትላለች፣ እኔም ለምን? ማለቴ አልቀረም። ትጊም ትቀጥላለች።

ቡና ቤት ውስጥ መጠጥ ማሻሻጥ አለ፣ በዚያ ላይ እግር ጥሎት የሚመጣን ወንድ ደፈር ብሎ ቤቱ ውስጥ ያሉትን በርካታ ሴቶች አሸንፎ፣ ሥርቶ ለማደር መጠጥ መጠጣት የግድ ነው። እንደዛም ከተገኘ ነው፤ ካልተገኘ በማግስቱ ጠዋት የሚላስ የሚቀመስ ላይኖር ይችላል። ቡና ቤት ውስጥ ለመሥራት ቤቶቹ በጣም ዘመናዊና ባለ ሀብት የሚመጣባቸው መሆን አለባቸው። አለበለዚያ እሷ ትሠራበት እንደነበረው ቺቺኒያ ዓይነት ከሆነ ወር ከገባ 10 ቀን በኋላ፣ ጤፍና ስንዴ ሲወደድ በብድር ለማደር የሚጠይቀው ይበዛል። ሀብታሞች የሚዝናኑበት ከሆነ ግን የኑሮ ውድነት፣ የክርስቲያን፣ የእስላም ጾም የለ ሁሌም አንድ ነው። በዚህ ላይ አብዛኞቹ ባላትዳሮች ስለሆኑ እዛው በአጭሩ ጣጣቸውን ጨርሰው ይሄዳሉ።

እንደ ትጊ አባባል እንዲህ ዓይነት ቦታ ለመግባት አንደኛ ዕድል፣ ሁለተኛ ደግሞ የቀማሾችን ፈተና በግሩም ሁኔታ ማለፍ ያስፈልጋል። ስለዚህ ሁሉም ሰው ተጠናቆ ሳይገባ፣ በግዜ ወጥቶ ወደ ሥራም ይሁን ወደ ቤቱ ወይም ሌላ ቦታ፣ በተቻለ መጠን ሀሳቡን አስቀይሮም ቢሆን፣ የሚሆነውን ሥርቶ መግባት ነው።

በጊዜ ለምን እንደምትመጣ ጠየኳት "የኑሮ ውድነቱ ወንዶች ኪስ ውስጥም ገብቷል፣ ምንም ኑሮ ቢወደድ በነገርዬው አይጨክኑም ነበር። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን ቡና ቤቶችም ባዶ ናቸው። መሸት አድርገን ብንወጣ ላይገኝ ስለሚችል በግዜ ወጥተን ሁሉንም እንሞክራለን …" አለችኝ።

ትጊ የመንገዱ ዝሙት አዳሪነት እንዴት ከቡና ቤቱ እንደሚሻል ሰፋ ያለ ማብራሪያ መስጠት ቀጠለች፤ በአብዛኛው የምታገኘው ሥራ ከአዳር ይልቅ ሾርት በጣም አሪፍ ነው፤ "ያኔ ደንበኞቼም ሆኑ እግረ መንገደኛው የሚጎበኙ ባለመኪኖች ናቸው። የኔ ቢጤው እግረኛ መሬት ደብዳቢ ምን ይፈይድልኛል። የውጭ ዜጎች ከሆኑ ዋጋዬን ከፍ አድርጌ እጠይቃለሁ፣ ወዳረፉበት ሆቴል ወይም ቤታቸው ይወስዱኛል፣ ግዴታዬን በሚገባ ከተወጣሁ ቲፕ ጨምረው ይሸኙኛል፣ ካላደረሱኝ ደግሞ በታክሲ ይሸኙኛል። አንዳንድ ግዜ መኪናቸው ውስጥ የሚፈልጉ አሉ። አበሾቹ ከሆኑ ግን አሁን ትንሽ ኑሮውም ስለተወደደ እስከ 100 ብርም ካገኘን እንሠራለን። ምክንያቱም አብዛኞቹ ባለትዳርና ቤተሰብ ያላቸው ስለሆኑ፣ ሆቴል ሲገቡም "መኪናችን ይታወቃል" ብለው ስለሚሰጉ ጨለም ወዳሉ ቦታዎች ሄጀ መኪናቸው ውስጥ ሥራዬን ሠርቼ እመለሳለሁ። እንዲህ እንዲህ እያልኩ ሰዓቴን በአግባቡ ከተጠቀምኩ፤ እንደ ቀኑ ሁኔታ ጥሩ ሥራ እሠራለሁ፤ ግን ባክሽ በእንትን የሚመጣ ገንዘብ በረከት የለውም" አለችና ወዲያው መለስ ብላ "ኧረ እግዚያብሔርዬ የተመሰገነ ይሁን! ይችንስ ማን አየበት"። "በዚህ ሥራ እግዚአብሔር ይተባበራል እንዴ?" ጥያቄን ለመጨረስ ዕድል ሳትሰጠኝ "መቼም ሠይጣን ብዬ አላመሠግን" አለችኝ።

በምሽት ሥራዋ በምታገኘው ገንዘብ ቤተሰቦቿን ትረዳለች። ሣምንቱን በሙሉ ባሉት ቀናት ደግሞ ሥራ እንደልብ አይገኝም፤ ቤት ኪራይ፣ ምግብ፣ ቀን በቀን የማይቀረው ጫትና ሲጃራ፣ ወደ ሥራ ከመሠማራቷ በፊት የምትጎነጨው መጠጥ፣ መጋጌጫ፣ የትራንስፖርት፣ … ወጪዋን ዘርዝራ አልጨረሰችም "ለሁሉም በገንዘብ ሳይሆን በዓይነት እየከፈልኩ ወጪዬ ቢቀንስልኝ" ስትል ምኞቷን ገለፀችልኝ።

ከተግባባኋት በኋላ ለረጅም ሰዓት አዋራችኝ፣ ዋሸቼ ከሥራዋ ያዘናጋኋት መሰለኝና ከጨዋታዬ ቀነስኩ፤ ጥቁር "አቶዝ" መኪና አጠገባችን መጣና ቆመ። መስታወቱን በሪሞት ከፈት አድርጎ ወደኔ ማየት ጀመረ፤ ጠጋ በይና አነጋግሪው አለችኝ። እሷ እንድታናግረው ገፋፋኋትና ፈንጠር ብዬ ምን እንደሚባባሉ ለማዳመጥ ሞከርኩ፤ ባይሰማኝም ተስማሙ መሰለኝ "እስከመለስ ካለሽ አገኝሻለሁ፣ ዛፓዎቹን ተጠንቀቂ" አለችና ገባች። እሷን ሲጨርስ ሊመለስብኝ ያሰበ

ይመስላል፤ "ስልክ ቁጥርሽን ስጪኝ" አለኝ፤ እንደሌለኝ ነግሬው ቀስ እያልኩ በተለምዶ ቴሌ መድኃኒዓለም እየተባለው ወደሚጠራው "ኤድናሞል" በእግሬ አመራሁ።

ዝሙት አዳሪዎቹ እየመሸ በሄደ ቁጥር እየተበራከቱ መጥተዋል፤ በየጥቂቱ ሜትሮች ርቀት ሁለት ሁለት እየሆኑ ስለቆሙ ጠጋ ብሎ የመቆም ድፍረቱን አጣሁ። የጎዳና ተዳዳሪዎች ለከፋና ጥሪ፣ የባለመኪኖች የአዳር ጥያቄ በሽ ነው። ዝሙት አዳሪዎች ምን ያድርጉ ሥራው በበቂ ሁኔታ ባይኖር እኮ ሊሠሩ አይወጡም ነበር እያልኩ የሴቶቹን አለባበስ መቃኘት ጀመርኩ።

አትላስ ሆቴል ደረስኩና እንደምንም አንዷ ጋር ጠጋ ብዬ ቆምኩ፣ እንዲህ እያልኩ ለሦስት ቀናት ቺቺኒያ፣ 22፣ ዑራኤል፣ ሳር ቤት፣ ፒያሳ፣ ከዝሙት አዳሪዎች ጋር አሳለፍኩ።

ዝሙት አዳሪዎቹ የሚሰጡት የአገልግሎት ዓይነትና ዋጋ እንደየሚቆሙበት አካባቢ ይለያያል፤ ገጠመኞቻቸው ግን ተመሳሳይ ነው።

መንገድ ዳር ላይ ቆመው ለሥራ የሚጠቀሙበት ገላቸውን በቅጡ የማይሸፍኑ ልብሶች ከመኖሪያ ሠፈራቸው ለብሰው አይወጡም። ምክንያቱም የሚኖሩበትንና የሚሠሩበትን አካባቢ አራርቀው ስለሚሠሩ ከቤታቸው ሲወጡ የተለመደ ለብሰው ብጣቂዎቻቸውን ደግሞ በቦርሳቸው አንግበው ነው።

ልብሳቸውን ለመቀየር ደግሞ በርካታ ተባባሪ አላቸው። ዋነኞቹ ደንበኞቻቸው "ላዳ" የከተማ ታክሲዎች ናቸው። የሚሠሩበት አካባቢ ያሉ የድርጅት የጥበቃ ሠራተኞችና ሱቆች ደግሞ ቀጣይ ሲሆኑ፣ እነሱ ከጠፉ ወደጨለማው ገባ ይላሉ። የተቀየረውን ልብሳቸውን በቦርሳቸው አንግበው ወደሥራ ይሰማራሉ። ከጂንስ ሱሪ ጀምሮ ገላን ብዙም የማያሳይ የተለመደ ልብስ ለብሰው የሚሠሩ ዝሙት አዳሪዎችም በርካታ ናቸው።

ከአትላስ ሆቴል መግቢያ ፊት ለፊት ቆማ ያገኘኋት ቤቲን ነው። የምተዋወቃቸው አብዛኞቹ ዝሙት አዳሪዎች ስማቸው ከሁለት ፊደል አያልፍም። ምናልባት ለራሳቸው ስያሜ ስለሚያወጡ ቀለል የሚል ስም እየመረጡ ይኾን ስል ወጌን ከቤቲ ጋር ቀጠልኩ።

"ሥራ ቀዝቅዟል አይደል?" ወሬ መጀመሬ ነበር። "ኧረ! ምን ይቀዘቅዛል የአዲስ አበባዎቹ አባ ወራዎች እንኳን ለኛ ለሌሎች ይተርፋሉ።" ድምጿ ጎርነን ያለ ነው። ስታወራ አንድ ቦታ ላይ አትቆምም ትንጎራደዳለች።

ቤቲ "ሥራው አልጠፋምም! አልቀዘቀዘምም!" ትላለች። ለምን በጊዜ እንደሚወጡ ጠየኳት። ከሌላው ጊዜ በተለየ በጊዜ የሚወጡት ከቡና ቤቶችና ስልክ እየጠበቁ ከመሥራት መንገድ ላይ ወጥቶ መሥራቱ የበለጠ ተመራጭ ኾነ? "ቤት እንከራያለን፤ ቀን ቀን እንተኛለን፣ አብስለን እንበላለን፣ ንፅኅናችንን በሚገባ እንጠብቃለን፣ የራሳችን አልጋ ላይ እንተኛለን፣ እንደፈለግን እንቅማለን፣ ስለዚህ ሴቱ ቡና ቤት ገብቶ መጠጥ ከማስተናገድ፣ ከመጠጣት፣ ሥራ ጠፍቶ አድሮ ጠዋት ከመንከራተት አምስትና ስድስት ሆኖ በአንድ አልጋ ከማደር ይኼን ይመርጣል። በዚህ የተነሳ አብዛኞቹ ወደዚህ ስለመጡ አመሻሽቶ መውጣቱ ብዙም ደስ አይልም፤ ባይሆን በጊዜ ወጥቶ ተሻምቶ ያገኙትን ሠርቶ መግባት ነው" አለችኝ።

ሥራው አዲስ ነገር አለመሆኑና፣ ሁሉም ሰው በይፋ እያወቀው የሚሠራ መሆኑን ቤቲ ትናገራለች። እሷም እንደሌሎቹ ጠቀም ያለና ከስድስት መቶ ብር በላይ ካልሆነ አዳር መሥራት አትፈልግም። ሾርት ከሆነ ቶሎ ወደ ቦታዋ ተመልሳ ለሌላ ሥራ በር ስለሚከፍትላት እሱን ትመርጣለች።

በነበርኩባቸው ቦታዎችና ባነጋገርኳቸው ሴቶች አገላለፅ፤ አሁን ባለው የገበያ ሁኔታ የግኘሁው ዋና ተጠቃሚዎች ባለትዳር ወንዶችና የውጭ ዜጎች ናቸው። አልፎ አልፎ ካልሆነ ትዳር የሌላቸው ወንዶች ብዙም አይጎበኟቸውም።

"አንዳንዶቹ ባለትዳሮች አምሽተውና መጠጥ ጠጥተው ወይም ወደቤታቸው ሲገቡ 'መኪናዬ ይታያል' ብለው ስለሚፈሩ ወደዚህ መምጣት ትተዋል፤ ከዛ ይልቅ ቀን በመንግሥትም ሆነ በግል ድርጅት የሚሠሩ ሴቶችን በተለያየ ነገር እየደለሉ ቅምጥ ማድረግ ይቀላቸዋል። ቀን ሌላ ሥራ እየሠሩ ማታ ሞባይላቸው ላይ እየተደወለላቸው የሚሠሩ በመበራከታቸው ሥራው ትንሽ ቀዝቅዟል። እንደድሮው ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ላይ ወጣ ብሎ ማግኘት የዕድል ጉዳይ ስለሆነ ነው በጊዜ የምወጣው።" ያለችኝ የፒያሳዋ እቴጌ ነበረች።

"እቴጌ" ልቅም ያለች ቆንጆ ናት። ከአንድ ሜትር ከ75 ሴንቲ ሜትር በላይ ቁመት ያላት ትመስላለች። የራሷ ይሁን የፈረንጅ ያልታወቀ ፀጉር ኸቅ አድርጋለች፤ ግን የማንም ይሁን የማን ለተከለ ሰውነቷና ለቅላቷ ውበት ሰጥቷታል። ወንዶች ባለመኪኖች ሲመጡ ጅንን ብላ ስለምታናግር ጓደኞቿ፤ "እቴጌ" የሚል ስም እንዳወጡላትና ስሟ እሱ ሆኖ እንደቀረ ገልፅችልኝ። የመጨረሻውን ሌሊት ፒያሣ ከእነ "እቴጌ" ጋር አሣለፍኩ።

ዝሙት አዳሪዎቹ፤ ለምን በጊዜ መውጣት እንደጀመሩ፣ ሥራው ቀዝቅዟል አልቀዘቀዘም፣ ፖሊሶች ለምን እንደሚያባርሯቸው ... ነገሮች ጥናት አጥንቶ ዙሪያ ገባውን አነጋግሮ ያስረዳቸውም ሆነ የነገራቸው የለም፤ በሂደት ከሚያዩትና ከሚገጥማቸው የራሳቸውን መላ ምት በመስጠት ግምታቸውን ብቻ ይናገራሉ።

የአብዛኞቹም አስተያየት በአነስተኛ ቡና ቤቶች ወይም "ባሮች" ውስጥ ያለው ገበያ በኑሮ ውድነት ምክንያት ቀንሷል፤ ስለዚህ በነዚህ ቦታዎች ሲሠሩ የነበሩ ገንፍለው ወደጎዳና ሲወጡና ከነበሩት ጋር ሲቀላቀሉ፤ ሥራውን እንደ አዲስ የሚቀላቀሉ ሲጨመሩ መብዛታቸውን ይገልፃሉ። ስለዚህ በጊዜ ተፎካክሮ ለመሥራት በጊዜ መጀመሩ አዋጪ ነው ይላሉ።

ከወጣት ወንዶች ይልቅ ባለትዳሮች ስለሚያዘወትሩበት ምክንያት የራሳቸውን መላምት ይሰጣሉ፤ ወጣቶቹ እንደፈለጋቸው የከተማውን የቤት ልጅ ነኝ ባይ ሲቀያይሩ ቢውሉ ጠያቂም ተቆጪም የላቸው።

ደፍሮ ቅምጥ መያዝ የሚፈራው፤ ሚስቱ ስትደብረውና ከሌላ ጋር መዳራት ሲያምረው፣ በቀላሉ መንገድ እዛው ከፍሎ ለመገልገል ወደ እነሱ ይሄድና ተንፈስ ብሎ ይመለሳል።

እነሱም እንዲህ ዓይነቱን ይፈልጉታል "ወጣቱ፤ እንደባለትዳሮቹ ማታ ገብቶ የሚታሰርበት እስር ቤት እና ተቆጪ ስለሌለው አንዴ ከያዘ አይለቅም፤ ትምክህተኛ ነው፤ ገንዘቤን እኮ ነው የከፈልኩት ስለሚል ደሞም ቢሆን

እስኪወጣለት ዕላዩ ላይ ማንጋት ይፈልጋል፤ ስለዚህ እኔ የምመርጠው ወይ ባለትዳር አሊያም የውጭ ዜጎችን ነው።" ትላለች እቴጌ።

"ስታነጋግሪ ባለትዳር ይሁን ነፃ በምን ታውቂያለሽ?" የኔ ጥያቄ ነበር። "አብዛኞቹ ወደዚህ ሲመጡ ለምን እንደመጡ ይታወቃል፤ መቼም ለጠበሳ አይመጡም ስለዚህ ቀለበታቸውን አያወልቁም። ቀለበት የሌላቸውም ቢሆኑ ተሰገብግበው የሚመጡት ባለትዳሮቹ ናቸው። ደፍረው አንድ ሰው ከጠየቁ እዛም እዛም በመጠየቅ የዓይነትና የዋጋ ንፅፅር አያደርጉም፤ ተደራድረው መጀመሪያ ካነጋገሩት ጋር ይሄዳሉ፤ ለምሳሌ ሚስቶቻቸው ውጭ ወይም ክፍለ ሀገር ሲሄዱ፤ ለቅሶ ወይም ዘመድ ቤት ሲያድሩ ተደብቀው መጥተው የሚገዙ አሉ" እቴጌ አያልቅባትም፤ በግምትና የምትነግረኝ ዝርዝር ስለኢንዱስትሪው መረጃ ለማቅረብ ከሷ የተሻለ አጥኚ (ሪሰርቸር) አያስፈልግም ታሰኛለች።

ስለውጭ ዜጎች ቀጠለች እቴጌ "እኛ በጣም ቆንጆዎች ነን፣ ሰውነታችን ከለሩም ቅርፁም ያምራል። በዚህ ላይ በጣም ስለምናስደስታቸውና ንፁኅዎች ስለሆንን ይመስለኛል ዶላራቸውን መዥረጥ እያደረጉ የሚገዙት" እቴጌ ጨዋታዋን ትቀጥላለች። ዝሙት ለሷ የሻጭና የገዥ ጉዳይ ነው፤ የውሀ፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የሠራተኛ ግብር ... የማይከፈልበት እግዚአብሔር የሰጣት ምርጥ ቢዝነስ ነው።

እንደ እነ እቴጌ ያሉት ቆነጃጅት፣ ለዓይን የሚያጓጓ ጭኖቻቸውን ከፋፍተው እምብርታቸውን በማትሸፍን ብጣቂ ጨርቅ ሸፍነው ጡቶቻቸውን ለተመልካች አጋልጠው፤ እጅግ ተኳኩለው በየመንገድ ዳሮቹ እየተንጎማለሉ እያጓጉ ሃሳብ የሚያስቀይሩ ዝሙት አዳሪዎችን ተቋቁሙ ወደቤቱ የሚገባ ባል ቢያመሽስ "ለምን አመሸህ?" ተብሎ ቁጣ ሊደርስበት ይገባል? እንኳን መጣልኝ በማለት "ተመስገን" ይባላል እንጂ!